


# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ ወታደራዊ መግለጫ

ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ/ም (ሜይ 19 ቀን 2009 ዓ/ም)

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ሰራዊት በሰሜን ጎንደር ጠገዴ ወረዳ ልዩ ስሙ ማይደሊ የተባለ አካባቢ በወያኔ ልዩ ሃይልና ሚሊሽያ ሰራዊት አባላት ላይ ጥቃት ፈጸመ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ሰራዊት ግንቦት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ማይደሊ ላይ በወያኔው ልዩ ሃይልና ሚሊሽያ ሰራዊት አባላት ላይ ባደረገው ድንገተኛ ማጥቃት 4 ገድሎ 2 አቁስሎ ትጥቅና መሳሪያዎች ከመሰል ጥይቶችና ቦንብ ጋር መማረኩን የኢሕአግ ወታደራዊ ኮሚቴ አስታውቋል፡፡

በዚህ ወቅት ብዛት ያላቸው የወያኔ ታጣቂዎች እግሬ አውጭኝ ብለው የሸሹ ሲሆን ለአካባቢዉ ነዋሪዎች የኢህአግን አላማና ፕሮግራም የሚያስተዋውቅ በራሪ ወረቀቶችም እንደተበተኑ የድርጅቱ ወታደራዊ ኮሚቴ ጨምሮ አስታውቋል፡፡

በተያያዘ ዜና በሰሜን ጎንደር ወልቃይት ወረዳ ቃፍታ መሲል ልዩ ስሙ እምባ ፍጭጭ የተባለ አካባቢ ንብረትነቱ የወያኔ የሆነ መጋዘን ማውደሙን የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ወታደራዊ መምሪያ አስታውቋል፡፡

ወታደራዊ መምሪያዉ የላከዉ ዜና እንደሚያመለክተዉ ይኸዉ የወያኔ የንግድ ተቋም የሆነዉ መጋዘን በኢህአግ ሰራዊት ሙሉ በሙሉ የወደመ ሲሆን ፤ የአካባቢዉ ነዋሪም በድርጊቱ በጣም መደሰቱን ከመግለጹም በላይ የኢህአግ ሰራዊትን እንኳን ደህና መጣችሁ ዘንድሮ አርሻ አናርስም ከእናንተ ጎን በመሰለፍ እንታገላለን ከማለታቸዉ ባሻገር ብዛት ያላቸዉ የአካባቢዉ ነዋሪዎች የድርጅቱን ሰራዊት እንደተቀላቀሉ አስታዉቋል፡፡

**አንድነት ሐይል ነው!!**
**የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር**

Email: info@eppfonline.org:      Website:  www.eppfonline.org